የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር
የትራንስፖርት ባለሥልጣን
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Transport & Communications
TRANSPORT AUTHORITY

680/2013

ቁጥር 77/ቀ/7/6/03/04
No.
ቀን 14/10/ ፪፻፬
Date 200

አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

ለትግራይ ብ/ክ/መ/ኮንስትራክሽን መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ
<u>መቀሌ</u>
ለአፋር ክልላዊ መንግስት ንግድና ኢን/ ትራ/ ኢንቨስትመንት ቢሮ
<u>ሠመራ</u>
ለአማራ ብ/ክ/መ/የንግድና ትራንስፖርት ቢሮ
<u>ባሕርዳር</u>
ለኦሮሚያ መንገዶችና ትራንስፖርት ኤጀንሲ
<u>ፊንፊኔ</u>
ለደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት የትራንስፖርት ቢሮ
<u>ሐዋሣ</u>
ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክ/መንግስት ንግድና ትራ/ኢን/ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ
<u>አሶሳ</u>
ለሶማሌ ክ/መ/የትራ/መን/ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ
<u>ጅጅጋ</u>
ለሐረሪ ሕዝብ ክ/መ/የትራንስፖርት ጽ/ቤት
<u>ሐረሪ</u>
ለጋምቤላ ሕ/ብ/ክ/መ/ንግድ ኢንዱስትሪ ቱሪዝም ትራንስፖርት ቢሮ
<u>ጋምቤላ</u>
ለድሬዳዋ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት
<u>ድሬዳዋ</u>

ጉዳዩ:- <u>በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች የወጣ መመሪያ መላክን ይመለከታል::</u>

የትራንስፖርት ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 468/97 በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት መመሪያዎችን፣ ደንቦችንና ስታንዳርዶችን በማዘጋጀትና በአገር አቀፍ ደረጃ ከክልሎች ጋር ምክክር በማድረግ በአስተያየት አያዳበረ በማፅደቅ በሥራ ላይ እንዲውል እያደረገ ይገኛል::

በዚሁ መሠረት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች የወጣ መመሪያን 7 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን መላካችንን እየገለጽን፣ በየመናኸሪያዎቹ መመሪያው ተፈፃሚ ስለመሆኑ ተገቢውን ክትትል እንዲደረግ እናሳስባለን::

ከሠላምታ ጋር

ካሣሁን ኃ/ ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለሕዝብ ትራ/አገል/ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት
- ለሕግ አገልግሎት የሥራ ሂደት
  <u>ትራንስፖርት ባለሥልጣን</u>

ስልክ ቁጥር Telepone 011-551-02-44
ፖ.ሣ.ቁ. P.O.Box 2504
ቴሌክስ Telex 21539 TA ET
ፋክስ Fax 011-551-07 15

መልስ በሚጽፉልን ጊዜ የእኛን ደብዳቤ ቁጥርና ቀን ይጥቀሱ
IN REPLYING PLEASE QUOTE OUR REFERENCE NUMBER & DATE

4

# በትራንስፖርት ባለስልጣን

## የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት

## በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች የወጣ መመሪያ

680/2013

ህዳር 2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## 1. መግቢያ

የተለዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የሕ/ክፍሎች እንደማንኛውም ዜጋ ሁሉ በሕግ ፊት እኩል ተጠቃሚነት ቢኖራቸውም በጉዞ ላይ የሚደረግላቸው ድጋፍ ባለመኖሩ የትራንስፖርት አገልግሎት በእኩል መጠቀም አልቻሉም በመሆኑም በሕዝብ ትራንስፖርት ከቦታ ቦታ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ሂደት የሚገድቡ በርካታ ችግሮችና ተፅዕኖዎች ሲደርሱባቸው ይስተዋላል፡፡ በመሆኑም የተለዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የሕ/ክፍሎች የትራንስፖርት አገልግሎት ለማግኘት በሚፈልጉበት ጊዜ በትኬት አቆራረጥ፣ በመናኸሪያ አገልግሎት፣ በጉዞ ላይ የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍና አገልግሎት አሠጣጥ እንዲሁም በትራንስፖርት አገልግሎት አሠጣጥ የሚያጋጥማቸውን ችግሮች በመለየት የአጭርና የረጅም ጊዜ የመፍትሔ አቅጣጫ ማስቀመጥ አስፈልጓል፡፡

የተለዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የሕ/ክፍሎች በትራንስፖርት አገልግሎት ከሚያጋጥማቸው ችግሮች ውስጥ

- ተሽከርካሪዎች ምቹ መግቢያና መውጫ የሌላቸው መሆኑ፣
- በተሽከርካሪው ውስጥ ተሳፍረው ሲሄዱ ሲደክማቸው የማረፊያ ቦታ አለመዘጋጀቱ፣
- የመፀዳጃና የተለያዩ መስተንግዶ አገልግሎት ለማግኘት አለመቻል፣
- ልዩ የዜብራ መተላለፊያ መንገዶች አጠቃቀም አለመዘርጋት፣
- ለአካል ጉዳተኞች ቅድሚያ የመስጠት ሕግ አለመኖሩ እና የሕዝብ ትራንስፖርት ተጠቃሚ የሆነዉ ሕብረተሰብም የተለዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ቅድሚያ አለመስጠት ተጠቃሽ ነው፡፡

በትራንስፖርት ዙሪያ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማሻሻል የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 468/97 መሠረት ስልጣን ተሰጥቶበታል፡፡ በዚህም መሠረት የተለዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች /ለሕፃናት፣ ለነፍሰጡር ሴቶች፣ ለአረጋውያን፣ መስማትና ማየት ለተሳናቸው የአካል ጉዳተኞች/ የትራንስፖርት ችግሮቻቸውን በአይነትና በመጠን እንደችግሮቻቸው አይነት ተለይተው ምቹ፣ ጥራትና አስተማማኝነት ያለው የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በሕዝብ የመንገድ ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሠጡ ግለሰቦች፣ ድርጅቶች፣ ማህበራትና ማንኛውም ትራንስፖርት ተጠቃሚ ህብረተሰብ የተለዩ ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው ይህ መመሪያ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

ስለዚህ የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የሕ/ክፍሎች የተሻሻለ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት፣ በመናኸሪያዎች፣ በፌርማታዎች፣ በመተላለፊያ መንገዶች ላይ የሕዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ግለሰቦች፣ ድርጅቶች፣ ማህበራትና የመንግሥት አካላት ተሳትፎና ልዩ ትኩረት የሚሹ በመሆኑ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## 2. ርዕስ

ይህ መመሪያ "በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የሕብረሰብ ክፍሎች የወጣ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. ዓላማ

የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ምቹ፣ ጥራቱን የጠበቀና ከአለማቀፋዊ ስታንዳርድ ጋር የተቀራረበ እና የሀገሪቱን አቅም ያገናዘበ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኙ ማስቻል ነው፡፡

## 4. ግብ

በሀገሪቱ ያሉ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ምቹና ጥራቱን የጠበቀ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡

## 5. ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ የአፈፃፀም መመሪያ

1. "ባለስልጣን" ማለት የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን እና በየክልሉ የተቋቋሙ የክልል ትራንስፖርት ባለስልጣን /ቢሮዎች/ ናቸው፡፡
2. የተለየ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የሕ/ክፍሎች ማለት ሕፃናት፣ አረጋውያን፣ ነፍሰጡር ሴቶች መስማት የተሳናቸው ማየት የተሳናቸውና እና አካል ጉዳተኞች ናቸው፡፡
3. ሊፍት(Lift) በዚህ መመሪያ እንደተጠቀሰው ሊፍት ማለት ለአካል ጉዳተኛ ለሆነ/ች ሰው ድጋፍ ሊሰጥ የሚችል ወደ ተሽከርካሪው ውስጥ የሚያስገባ መሳሪያ ነው፡፡ ይህ ማለት ከተሽከርካሪው የሰው መግቢያ በር ላይ ወደ መሬት የሚዘረጋ ወይም የሚወርድ ሆኖ ለዊልቸር ወይም አካል ጉዳተኛውን የተሸከመ ቁስ አካል መውጫና መግቢያ ሊያገለግል የሚችል ነው፡፡

## 6. *የተፈፃሚነት ወሰን*

ይህ መመሪያ በመላ ሀገሪቱ በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጡ ግለሰቦች፣ ድርጅቶች፣ ማህበራትና በሌሎች የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል::

## 7. *በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች በሚመለከት የወጣ መመሪያ:-*

### 7.1 *ማየት ለተሳናቸው ሊደረግላቸው የሚገባ ድጋፍ*

1. ትኬት ቆራጮች በማይክራፎን እየተጠቀሙ ለተጓዥ መንገደኞች እና ማየት ለተሳናቸው የተሳፈሩበት ተሽከርካሪ የደረሰበትን ቦታ፣ ቁርስ፣ ምሳ፣ እና ራት የት እና መች መብላት እንዳለባቸው መረጃ መስጠት አለባቸው:: መፀዳዳት ቢያስፈልጋቸው ደግሞ አሽከርካሪው ሆቴል አጠገብ ተሽከርካሪ በማቆም መፀዳጃ ቤት እንዲጠቀሙ ማድረግ አለበት:: ረዳቱ ደግሞ ከተጠቀሙ በኋላ ወደ ተሽከርካሪው መመለሳቸውን ማረጋገጥ አለበት:: በተጨማሪም ረዳቱ መረጃ በመስጠት መተባበር አለበት::
2. ማየት ለተሳናቸው የእግረኛ መንገድ ጠብቀው መጓዝ የሚያስችል መስመር መሠራት አለበት፣ የሚሠራውም በመናኸሪያዎችና በዋና ዋና የከተማ ውስጥ መንገዶች ሲሆን ከመንገዱ የቀኝ ጠርዝ በ50 ሳ.ሜ. ርቀት ላይ መስመር መሠራት አለበት፣
3. በከተማ ውስጥ በአደባባዮችና በተለያዩ ዜብራ መተላለፊያዎች ማየት የተሳናቸው በቀላሉ ለመተላለፍ የሚያግዝ ድምፅ የሚሰጥ መሣሪያ መንገድ ዳር በቀኝ ጠርዝ 50 ሳ.ሜ ርቀት ላይ መገጠም አለበት:: ይኸውም በየአንድ ደቂቃ ልዩነት ድምፅ የሚያሰማ መሆን አለበት፣
4. በአውቶብስ ፌርማታዎች በእየፌርማታው የሚቆሙ አውቶብሶች ቁጥር፣ መነሻና መድረሻ ቦታ ማየት ለተሳናቸው ሊያነቡት የሚችሉበት ፅሁፍ መዘጋጀትና መለጠፍ አለበት:: ይኸውም ከመንገድ የቀኝ ጠርዝ አንድ ሜትር ርቀት ላይ ሆኖ የድምፅ መስጫ መሳሪያ የተገጠመበት ቦታ በአንድ ላይ ሆኖ በአንድ ሜትር ከፍታ ላይ መለጠፍ አለበት::
5. ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል፣ ማየት የተሳናቸዉ መረጃ ፈልገው ሲጠይቀት መረጃ የመስጠትና የፈለጉትን እርዳታ የመስጠት ግዴታ አለበት::

6. ትኬት ቀራጩና ረዳቱ ከመኪና ወርደው ማየት የተሳናቸውን ዜጎች የፈጉት መኪና ሳይ ቅድሚያ የመስጠት የማሳፈር ግዴታ አለባቸው::
7. በእየመናኸሪያው ያሉ ተራ አስከባሪዎችና ተቆጣጣሪዎች ማየት የተሳናቸውን ከመናኸሪያው በር ተቀብለው ወደሚፈልጉት ተሽከርካሪ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው::
8. የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ አካላት በሙሉ ማየት ለተሳናቸዉ መረጃ የመስጠትና የመተባበር ግዴታ አለባቸው::
9. የማኅበራት ቅጥር ሠራተኞች ማየት ለተሳናቸው መረጃ የመስጠት ግዴታ አለባቸው::

## 7.2 *<u>መስማት ለተሳናቸው ሊደረግላቸው የሚገባ ድጋፍ</u>*

1. ማህበራት መስማት ለተሳናቸው ትኬት በሚቆርጥበት ጊዜ ሙሉ መረጃ በመያዝ ማንበብና መፃፍ የሚችል ወይም የማይችል መሆኑን በመለየት ማንበብ ለሚችለው የተሣፋሪበት ተሽከርካሪ ውስጥ የጉዞውን ፕሮግራም በፊት ለፊት በሚታይበት ቦታ white board ላይ መፃፍ አለበት:: ማንበብ ለማይችለው ማህበራት ሁሉም ትኬት ቆራጮች በተቻለ መጠን በምልክት መረጃ እንዲሰጡ እና መረጃ እንዲያገኙ መደረግ አለበት::
2. በከተማ ውስጥ በአደባባዮችና በተለያዩ ዜብራ መተላለፊያዎች መስማት ለተሳናቸው በቀላሉ ለመተላለፍ የሚያግዝ የትራፊክ መብራትና ምልክት መደረግ አለበት:: በተጨማሪም የመብራት ምልክት ለተሽከርካሪው በሚሠጥበት ጊዜም መስማት የተሳናቸው መንገድ ውስጥ ከገቡ ቅድሚያ መሰጠት አለበት::

## 7.3 *<u>ለአካል ጉዳተኞች ሊደረግላቸው የሚገባ ድጋፍ</u>*

1. ለአካል ጉዳተኞች ምቾት የሚሰጥ መቀመጫ ከሾፌሩ ኋላ ከአንድ እስከ አራት መቀመጫ ወንበሮች እንዲያገኙ መደረግ አለበት፣ ተቀምጦ መሄድ የማይችል የአካል ጉዳተኛ ከሆነ እና መተኛት የሚያስፈልገው ከሆነ የመጨረሻ ወንበር ላይ ወይም እሱ የመረጠውን ወንበር እንዲያገኝ መደረግ አለበት:: ሆኖም በያዘው ወንበር /መቀመጫ/ ልክ ከአንድ ወንበር በላይ ከተጠቀመ የተጠቀመው ወንበር ብዛት በታሪፉ ተባዝቶ ተገቢውን ታሪፍ ይከፍላል::
2. በከተማ ውስጥ በአደባባዮችና በተለያዩ ዜብራ መተላለፊያ መንገዶች ላይ አካል ጉዳተኞች በቀላሉ ለመተላለፍ የሚያግዙ የትራፊክ መብራትና ምልክቶች መደረግ

አስበት። የመብራት ምልክት ስተሽከርካሪው በሚፈቅድበት ጉዜ አካል ጉዳተኛው መንገድ ውስጥ ከገባ ቅድሚያ መሰጠት አስበት።

3. ማንኛውም የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ተሽከርካሪ ስአካል ጉዳተኞች መግቢያ የሚያገለግል ስሁዊልቸር (wheel chair)መግቢያ የአውቶቡስ ስሪት ከፍና ዝቅ የሚል አውቶቡሶች ሊፍት (Lift)እንዲኖራቸው መደረግ አስበት፣
4. ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡና የሚሠሩ አውቶብሶች ስአካል ጉዳተኞች በሁልቸር ስመውጣትና ስመግባት የሚያስችል Rack lift/escalator ያስው መሆን አስበት፣

## 7.4 *ስአረጋውያን ሊደረግላቸው የሚገባ ድጋፍ*

1. ተሣፋሪዎች በትኬት ቀጥራቸው መሠረት የሚቀመጡ ቢሆንም ስአረጋውያን ግን ተሣፈሪዎች በሙሉ /ልዩ ድጋፍ ከሚያስፈልጋቸው ተሣፈሪዎች በስተቀር/ የተሻስ መቀመጫ የመስጠት ግዴታ አስባቸው። በዚህም መሠረት ትኬት ቆራጩ ዘግይቶ የመጡ አረጋውያንን ስማስቀመጥ የቦታ ቅያሪ በጠየቀ ጊዜ ተሣፈሪዎች የመተባበርና ስአረጋውያን ቅድሚያ የመስጠት ግዴታ አስባቸው።
2. የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ረዳቶች /ትኬት ቆራጮች/ አረጋውያን ሲሳፈሩና ሲወርዱ መደገፍ አስባቸው።
3. አረጋውያን የሚጓዙበት የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ መንገድ ላይ በሚያድርበት ጊዜ አሽከርካሪው ወይም የአሽከርካሪው ረዳት ጠዋት መቀስቀስ አስበት።
4. በጉዞ ሰዓት አሽከርካሪው፣ የአሽከርካሪው ረዳት እና ትኬት ቆራጭ ስአረጋውያን እንክብካቤ ማድረግ አስባቸው።

## 7.5 *ለነፍሰ ጡር ሴቶች ሲደረግላቸው የሚገባ ድጋፍ*

1. በማንኛውም የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ነፍሰ ጡር ሴቶች በሚጓዙበት ጊዜ ለከፍተኛ ሙቀት ወይም ለነፋስ የማይጋልጥ ቦታ መቀመጥ አለባቸው።
2. ከተሽከርካሪው ሲወጡ እና ሲወርዱ መደገፍ አለባቸው።
3. ለነፍሰ ጡር ሴቶች በሚጓዙበት ጊዜ ልዩ እንክብካቤ መደረግ አለበት።
4. ነፍሰ ጡር ሴቶች በሚጓዙበት  ጊዜ የያዙትን ሻንጣ/መገልገያ እቃ የአሽከርካሪው ረዳት ከተሽከርካሪው አውርዶ ማስረከብ አለበት።

## 7.6 *ለህፃናት ሲደረግላቸው የሚገባ ድጋፍ*

1. ህፃናት ከተሽከርካሪው ሲወርዱ መኪና እንዳይገጫቸው የአሽከርካሪው ረዳቶች ድጋፍ ማድረግ አለባቸው።
2. ህፃናት ሲሳፈሩ እንዳይወድቁ የአሽከርካሪ ረዳቶች እጃቸውን ይዞ ማሳፈር አለባቸው።
3. ህፃናት ለነፋስና ሙቀት የተጋለጠ ቦታ እንዳይቀመጡ መደረግ አለበት።
4. ህፃናት በሚጓዙበት ጊዜ እንክብካቤ ሲደረግላቸው ይገባል።
5. ገንዘብ ተቀባይ እረዳቱና አሽከርካሪው ለሕፃናቱ መረጃ እና ቅድሚያ በመስጠት እንዲሳፈሩ ማድረግ አለባቸው።

## 7.7 *የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው /ማየት ለተሳናቸው፣ መስማት ለተሳናቸው፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋዊያን፣ ለነፍሰጡር ሴቶችና ለህፃናት/ ሲደረግላቸው የሚገባ ድጋፍ*

1. የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች በማንኛውም የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ሰልፍ ሳይሰለፉ /ተራ ሳይጠብቁ/ ቅድሚያ ትኬት እንዲያገኙ መደረግ አለበት፣
2. የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች በማንኛውም የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ሲሄዱ ማንም ሰው ተሽከርካሪው ውስጥ መግባት ሳይጀምር ቅድሚያ ተሰጥቷቸው መቀመጫ እንዲያገኙ መደረግ አለበት፣
3. የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ይዘውት የሚጓዙ ዕቃ/ሻንጣ/ ከመናኸሪያው በር ጀምር እስከ ተሽከርካሪው ድረስ ማጓጓዝ እና የመጫንና ማውረድ አገልግሎት ያለምንም ክፍያ ማህበራት በቀጠሯቸው ሠራተኞች አገልግሎት እንዲያገኙ መደረግ አለበት። ይኸውም ማህበራት ከትኬት መቁረጫ ቦታ ጀምር የተለየ ድጋፍ

ስሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መረጃ በመያዝ አገልግሎት እንዲያገኙ ሰሠራተኞች በቅድሚያ ማሳወቅ አለባቸው፣

4. በህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰሚሠጡ የተለየ ድጋፍ ስሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የሚደረጉ ልዩ ድጋፎች ቅድሚያ መቀመጫ ወንበር እንዲያገኙ እና አስፈላጊው ድጋፍ እንዲደረግላቸው በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በግልፅ ቦታ ላይ በመለጠፍ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማሳሰብና ማሳወቅ አለበት፣
5. የትራንስፖርት አገልግሎት ቀደም ብሎ እንዲደረጅላቸው በማንኛውም የኤሌክትሮኒክ ሚዲያ ተጠቅመው ያሳወቁት የህዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተር፣ ድርጅት ወይም ማህበር ሰጉዞው የሚያስፈልጋቸውን የትራንስፖርት ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 8. <u>*የማሻሻል ወይም የመሻር ሥልጣን*</u>

ይህን መመሪያ ሰማሻሻል ይሁን ሰመሻር ሥልጣን ያለው የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ነው፡፡

## 9. <u>*መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ*</u>

ይህ መመሪያ ከ __________ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

